**በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ**
**የዩናይትድ ስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት**

| | | |
|---|---|---|
| ጆን ዶ ፣ ሌላው መጠሪያው ኪዳኔ፣<br>c/o Electronic Frontier Foundation<br>815 Eddy Street<br>San Francisco, CA 94109<br><br>ከሳሽ<br><br>በ.<br><br>የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራስያዊ ሪፑብሊክ<br>የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር<br>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር<br>ፖ.ሳ.ቁ 393<br>አዲስ አበባ<br>ኢትዮጵያ<br>ተከሳሽ | ) | ፍትሀ ብሄር ቁ.: ________________<br><br>**አቤቱታ**<br><br>**የፍርድ ሸንጎ ( "ጁሪ") ተጠይቋል** |

**አቤቱታ**

1. ከሳሽ ጆን ዶ ፣ ሌላው መጠሪያው ኪዳኔ ("ከሳሽ" ወይም "አቶ ኪዳኔ") የሚከተለው ተፈፅሟል በማለት ይኽንን ክስ በኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ሪፑብሊክ ("ተከሳሽ" ወይም "ኢትዮጵያ") ላይ አቅርቧል:

**የመጀመሪያ ደረጃ መግለጫ**

2. ይኽ፣ የአሜሪካዊ ዜጋ የግል ህይወት በ "ሰበርባን" ሜሪላንድ በሚገኘው መኖሪያ ቤቱ ውስጥ በስልክ መጠለፍንና መደፈርን የሚቃወም / የሚፈታተን፣ ግልፅ ያለ የክስ ጉዳይ ነው። በዚህና በሌሎች ተራ የስልክ ጠለፋዎች መካከል ያለው ልዩነት፣ በዚህኛው ላይ ጠለፋው የተካሄደው በኢትዮጵያ መንግስት መሆኑ ብቻ ነው።

3. አቶ ኪዳኔ ኢትዮጵያ የተወለደ ሲሆን፣ በ ዩ ኤስ ውስጥ ከ 22 ዓመታት በላይ የኖረ የዩ ኤስ ዜጋ ነው።

4. በኦክቶበር 2012 (እ.ኤ.አ) መጨረሻ እና በማርች 2013 (እ.ኤ.አ) መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ተከሳሽ የአቶ ኪዳኔን የጭን ኮመፒዩተር፣ ፊንስፓይ በመባል በሚታወቁ የኮምፒዩተር ፐሮግራሞች እንዲለከፍ በማድርግ ቢያንስ

በደርዘን በሚቆጥሩ የአቶ ኪዳኔ የስካይፕ[1] የኢንተርኔት የስልክ ጥሪዎች ላይ በሚስጥር የድምፅ ቅጂ ፈፅሟል፣ በአቶ ኪዳኔ የተላኩ በርከት ያሉ ኢ-ሜይሎችን በከፊል ወይም በሙሉ ገልብጧል፣ እንዲሁም የአቶ ኪዳኔ ወንድ ልጅ ለዘጠነኛ ክፍል የታሪክ ትምህርቱ ከስፖርትና ከመድሀኒት ታሪክ ጋር የተያያዘ የድረ ገፅ ፈለጋን ገልብጧል።

5. ከዚህ በታች ቀጥሎ እንደተገለፀው፣ ከሳሽ ኮምፒዩተሩ የተለከፈው በተከሳሽ ወይም በተከሳሽ ወኪል አማካኝነት በተላከና ቀጥሎም ለከሳሽ "ፎርዎርድ" በተደረገ የማይክሮሶፍት ሰነድን ባባሪነት በያዘ ኢ-ሜይል ምክንያት ስለመሆኑ መረጃ የደረሰው ከመሆኑም በላይ ያምንበታል። ከዚያም አባሪው ሌላ ሚስጥራዊ "ክላየንት" ፕሮግራም ኮምፒዩተሩ ላይ እንዲጫን አደረገ። ቀጥሎም የተጫነው "ክላየንት" ፕሮገራም የከሳሹን ኮምፒዩተር ሙሉ በሙሉ እቁጥጥሩ ስር አዋለ። ከዚያ በሁዋላ ከሳሽን እና የቤተሰቡ አባላትን ጨምሮ፣ የኮምፒዩተሩ ተጠቃሚዎችን እንቅስቃሴዎች እየገለበጠ፣ በሙሉም ባይሆን አንዳንዶቹን ኢትዮጵያ ወደሚገኝ "ሰርቨር" መላክ ጀመረ።

6. ይሕንን ስለላ ያከናወኑት ፕሮግራሞች በጋራ ፊንስፓይ በመባል ይታወቃሉ። ፊንስፓይ፣ የመሳሪያዎቹ ተገልጋይ ሳያውቅ፣ ኮምፒዩተሮችን እና የእጅ ስልኮችን ጨምሮ፣ ከኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ላይ መረጃዎችን ለመከታተልና ለመሰብሰብ የሚያገለግል ስርዓት ነው።

7. ሲትዘንላብ ካናዳ በቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ ዘንደ ባለው የመንክ የሉላዊ ጉዳዮች ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኝ ፈርጀ ብዙ ቤተ ምርምር / ቤተ ሙከራ ነው። ሲተዘን ላብ በዲጂታል መገናኛ፣ በሉላዊ ደህንነት፣ እና በሰብዓዊ መብቶች በሚገኛኙበት መስቀለኛ ላይ በሚከናወን ከፍተኛ ምርምር እና ዕድገት ላይ ያተኩራል።

8. በዓለም ዙሪያ ያሉ የሰብዓዊ መብቶችና የዴሞክራሲ ተሟጋቾችን ለመሰለል መንግስታት እንዴት በፊንስፓይ እንደሚጠቀሙ ሲትዘንላብ መርምሯል። በማርች 13፣ 2013 (እ.ኤ.አ)፣ ሲትዘንላብ ስለ ፊንስፓይ መንሰራፋት ዘገባ አሰራጭቷል። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝ የፊንስፓይ "ማስተር ሰርቨር"ን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችል ዝርዝርን ያካተተ የኢትዮጵያን የፊንስፓይ አጠቃቀም የሚገልፅ ክፍል ይዟል። ከዚህ በታች በዝርዝር እንደተገለፀው፣ በሲትዘንላብ ዘገባ ውስጥ የተገለፀው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው "ማስተር ሰርቨር" ያው የአቶ ኪዳኔ ኮምፒዩተር ላይ የሚገኘውን "ታርጌት ኢንስቶሌሽን" የሚቆጣጠረው ሰርቨር ነው።

---

[1] ስካይፕ፣ በማይክሮሶፍት የተዘጋጀ የድምፅ- አይ ፒ የግንኙነት አገልግሎት ነው። የስካይፕ አገልግሎት፣ ተጠቃሚዎች በድምፅ (በድምፅ ማጉያ)፣ ቪዲዎ (በ ድረ-ካሜራ)፣ እና ቴክስት ( በ ፈጣን መልዕክት መላኪያ) አማካኝነት በኮመፒዩተራቸው ግንኙነት እንዲያካሂዱ ይፈቅድላቸዋል።

9. ማርች 18፣2013 (እ.ኤ.አ) አካባቢ፣ ከሲትዘንላብ ዘገባ አምስት ቀን በሁዋላ፣ በአቶ ኪዳኔ ኮምፒዩተር ላይ የተጫነው "ታርጌት" ፊንስፓይ እንዲነሳ ተደረገ። ይሁንና፣ ግልፅ በሆነ የለስላስጌ ብልሽት ምክንያት የፊንስፓይ ከሩቅ የማንሳት ሂደት ከአቶ ኪዳኔ ኮመፒዩተር ላይ ሙሉ በሙሉ የለስላስጌውን ርዝራዥ ለማስወገድ አልቻለም።

10. በአቶ ኪዳኔ ኮምፒዩተር ላይ የተጫነው ፊንስፓይ ቢያንስ ለአራት ወራት ተኩል፣ ከኖቬምበር 2012 መጀመሪያ አካባቢ ጅምሮ እስከ ማርች 2013 (እ.ኤ.አ) አጋማሽ ድረስ፣ ይሰራ ነበር። በነዚህ ጊዜያት ውስጥ ሁሉ፣ ኢትዮጵያ የአቶ ኪዳኔን እንቅስቃሴዎች ወደ ኢትዮጵያው "ሰርቨር" በኩል በማስተላለፍ፣ በአቶ ኪዳኔ ኮምፒዩተር ላይ ያልተገደበ ተደራሽነት እንደነበራት ከሳሹ መረጃ አለው፣ ያምንበታልም።

11. አቶ ኪዳኔ፣ ኢትዮጵያ የእርሱን ግንኙነቶች በማግኘቷ እና ከዚሁ ጋር የተያያዙ የብቻነት መብቱ ጥሰቶች መስመር የሳቱ እና ህጋዊነት የሌላቸው ስለመሆናቸው መግለጫ እንዲሰጥ ይሻል።

12. ኢትዮጵያ በብቻነቱ ላይ ጣልቃ በመግባቷ በ "ዋየርታፕ" የህግ ደንጋጌ መሰረት ህግ የሚወስንለትን የጉዳት ካሳ እና (መደበኛ) የጉዳት ካሳ፣ አቶ ኪዳኔ በተጨማሪ ይሻል።

## የስልጣን ክልል እና የመዳኛ ስፍራ

13. ይኸ ፍርድ ቤት በ ዩ ኤስ ኮድ 28 § 1330 መሰረት፣ በ "ፎሪን ሶቨሪን ኢሙዩኒቲስ" የህግ ድንጋጌ ( "ዘ 'ፊሳ' ")፣ እንዲሁም በዩ ኤስ ኮድ 28 § 1602 ና ተከታዮቹ መሰረት ፣ በዚህ አቤቱታ ውስጥ ተፈፅሟል በተባለው መሰረት፣ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ የግዛት ክልለ ውስጥ ከውል ውጭ በሆነ ምክንያት ለደረሱ ጉዳቶች፣ በጉዳዩ እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ ላይ ግላዊ ("ፐርሶናል") ስልጣን አለው። በዩ ኤስ ኮድ 28 §1608 (a) መሰረት ለኢኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ መጥሪያ ይሰጠዋል።

14. በተለይም፣ ተከሳሽ፤ ከማንኛውም በዩናይትድ ስቴትስ የግዛት ክልል ውስጥ በባዕድ መንግስቱ ወይም በማኝኛውም የዚያ ባዕድ መንግስት ሰራተኛ ወይም ባለስልጣን የስልጣን ወይም የስራ ክልል ውስጥ በተፈፀመ ወይም ሳየፈፀም በቀረ ድርጊት ምክንያት ለተፈጠረ የግል ጉዳት ወይም ሞት፣ ወይም በንብረት ላይ ለደረስ ጉዳት ወይም ንብረትን ማጣት፣ የገንዘብ ጉዳት ካሳ ከሚሻ ከስ ነፃ የመሆን መብት ("ኢሚዩኒቲ") የሌለው ባዕድ መንግስት በመሆኑ፣ እና የይገባኛል

ጥያቄው "ዲስክሬሽናሪ" በሆነ ስልጣን ህጋዊ አጠቃቀም ላይ ያልተመሰረተ ስለሆነና "ከተንኮል-አዘል ክስ ("ፐሮሴክዩሽን")፤ በህግ ስርዓቱ አላግባብ ከመገልገል፣ ወይም በሚታይም ሆነ በሚደመጥ መንገድ ስም ከማጥፋት፤ ያልሆነውን እንደ ሆነ ከማስመሰል፣ ከማታለል ወይም በውል መብቶች ውስጥ ጣልቃ ከመግባት የማይመነጭ ስለሆነ፣ ይኽ ፍርድ ቤት በኢትዮጵያ ፌድራል ዴሞክራቲክ ሪፑበሊክ ላይ በ 28 ዩ ኤስ ሲ §§ 1603 (a)፣ 1605 (a) (5), እንዲሁም 1606 መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው።

15. በዚህ አቤቱታ ውስጥ እንደተባለው፣ ተከሳሽ ወይም የተከሳሽ ባለስልጣናት፣ የ"ዋየርታፕ አክት" 18 ዩ ኤስ ሲ §§ 2511፣ 2520 ን በመጣስ፣ በዩናይትድ ስቴትሰ ወስጥ በሚኖረው እና የ ዩ ኤስ ዜጋ በሆነው ከሳሽ ላይ፣ በዩናይትድ ስቴትስ የግዛት ክልል ውስጥ በቤቱ ውስጥ፣ ከውል ውጭ፣ ብቻነቱን በመድፈርና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የከሳሹን ግንኙነቶች በመጥለፍ በከሳሹ ላይ የግል ጉዳት አድርሶበታል።

16. በተለዋጩ፣ ይኽ ፍርድ ቤት፣ "ከዩናይትድ ስቴትስ ህገ መንግስት፣ ህጎች እና ስምምነቶች በሚመነጩ የፍትሀ ብሄር ነክ ጉዳዮች ላይ በሙሉ የመጀመሪያ ስልጣን" ለዲስትሪክት ፍርድ ቤት በሚሰጠው 28 ዩ ኤስ ሲ § 1331 መሰረት፣ ይኽንን ጉዳይ የመስማት ስልጣን አለው።

17. ከዚህም በላይ በ 28 ዩ ኤስ ሲ § 1367 (a) መሰረት ተከሳሹ ባቀረባቸው ተጨማሪ የይገባኛል ጥያቄዎች ላይ ፍርድ ቤቱ ተጨማሪ ( "ሰፐልሜንታል") ስልጣን አለው።

18. ተከሳሹ የባዕድ መንግስት ስለሆነ በ ዩ ኤስ ሲ 28 § 1391 (f ) መሰረት በዚህ የዳኝነት ክልል ውስጥ መዳኘት አግባብነት አለው።

## ተሚጋቾች

19. ከሳሽ ጆን ዶ፣ ሌላው መጠሪያው ኪዳኔ፣ ባሁኑ ጊዜና፣ ይኽንን አቤቱታ በሚመለከቱ ሌሎች ጊዜያት በሙሉ ሲልቨር ስፐሪንግ፣ ሜሪላንድ ውስጥ የኖረና እና የሚኖር፣ ኢትዮጵያ የተወለደ ዩናይትደ ስቴትሰ አፍ አሜሪካ ዜጋ ነው።

20. ማንነቱ ሳይታወቅ ጉዳዩን ለመቀጠል እንዲፈቀድለት ከዚህ ክስ ጎን ለጎን ከሳሽ ባቀረበው ጥያቄ ውስጥ በዝረዝር እንደተገለፀው፣ በዩናይትደ ስቴትስ ውስጥም ሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦቹን ደህንነት ለመጠበቅ፣ በ ኢትዮጵያ ዲያስፖራ ውስጥ ኪዳኔ በሚለው መጠሪያ ይጠቀማል።

21. ተከሳሹ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሬፑብሊክ፣ በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚገኝ ሉዓላዊ መንግስት ነው።

## <u>የክሱ ፍሬነገር</u>

## በ ኢትዮጵያ መንግስት የሚፈፀም የተቃውሞ አፈና

22. ኢትዮጵያን በሚመለከተው የዩናይትደ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር የሰብዓዊ መብቶች አተገባበር የ 2012 (እ.ኤ.አ) ዘገባ መሰረት "[ኢትዮጵያ ውስጥ] አጅግ ጎልተው የሚታዩት የሰብዓዊ መብት ችግሮች፣ የታወቁ የተቃዋሚ የፖለቲካ ሰዎችን፣ "አክቲቪስቶችን"፣ ጋዜጠኞችን እና "ብሎገሮችን፣ ፓለቲካን መነሻቸው ባደረጉ ክሶች አማካይት በመክሰስና ("ትራያልስ") እና በፍርድ በማስቀጣት፣ ራስን የመግለፅ እና የመሰብሰብ መብቶችን መገደብን እና በህትመት መገናኛዎች ላይ ያለውን ገደብ ማጠናከርን ያካትታል []።" [2]

23. ሜይ 16፣ 2012 (እ.ኤ.አ) በተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ አምኔሲቲ ኢንተርናሽናል " የኢትዮጵያ ህዘቦች አብዮታዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ኢትዮጵያን ከሁለት አሰርት ዓመታት በላይ ገዝቷል። (የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚነስትር መለስ) ዜናዊ መንግስት፣ በታቀደ ዘዴ (በተሰላ መንገድ) የተቃዋሚ አባላትን እና ጋዜጠኞችን በማሰር፣ ባልታጠቁ ሰላማዊ ሰልፍ አድራጊዎች ላይ ተኩስ በመክፈት፣ እና የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ለመሸርሸር በመንግስት ሀብት በመጠቀም፣ በሀገሪቱ ውስጥ በሃሳብ መለየትን ("ዲሴንት") ለመጨፍለቅ ሞክሯል" በማለት ዘግቧል።[3]

24. የኢትዮጵያ መንግስት በውጭ ሀገርም ይሆን በሀገር ውስጥ፣ የፖለቲካ ተቃውሞን ለመሸርሸር ይፈልጋል። ልምሳሌ፣ የኦክተበር 11፣ 2012 (እ.ኤ.አ) የ"ኖርዊጅያን በሮድካስቲንግ ኮረፖሬሽን {ኤን አር ኬ} ዘገባን በአጭሩ በገለፀው የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን ድረ ገፅ መሰረት፣ በስደተኞች ላይ የሚካሄድ ስለላ መጠነ-ሰፊ ነው። አብዛኛውን

---

[2] United States Department of State, Country Reports on Human Rights Practices for 2012, http://www.state.gov/j/drl/rls/hrrpt/humanrightsreport/index.htm?year=2012&dlid=204120 (last visited December 20, 2013).

[3] Amnesty International, http://www.amnestyusa.org/news/press-releases/amnesty-international-urges-president-obama-to-speak-up-about-repression-human-rights-abuses-in-ethi (last visited December 20, 2013).

ጊዜ ስለላው የመጡበትን ሀገር ያገዛዝ ስርዓት ስለሚቃወሙ ስደተኞች መረጃ ለማገኘት ይሞክራል። ይኸንን የ "ኖርዌጂያን ፖሊስ ሴኩሪቲ ሰርቪስ ("ፒ ኤስ ቲ") ያረጋገጠ ሲሆን፣ አክሎም በርካታ ሀገራት፣ በተለይም በግጭት ውስጥ ያሉ ሀገራት፣ ስደተኞች ላይ የስለላ ተግባር ያካሂዳሉ ብሏል። አስሎ የሚገኘው የፀረ-ዘረኝነት ማዕከሉ ሩኔ በርግለንድ ስቲን፣ እንዲህ ይላል፡ በ 2204/2205 (እ.ኤ.አ) በሰበሰብኩት መረጃ መሰረት፣ በኢትዮጵያወያን ስደተኞች ላይ የሚካሄደው ስለላ በተደራጀ ዘዴና በተሟላ ሁኔታ የሚካሄድ ነው። መጠነ-ሰፊነቱ ዓይን ያወጣ ነው። ይኸ ለረዥም ጊዜ ሲካሄድ ስለመሆኑ እና፣ ስለላው ኖርዌይ ውስጥ ሊያስከትል ከሚችለው ህጋዊ ውጤት ጋር አለመዛመዱን ይናገራል።[4]

25. የኢትዮጵያ መንግስት የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ከሚከታተልበት መንገድ አንዱ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎችን መሰለል ("ሰረቬላንስ") ነው። "ፍሪደም ኦን ዘ ኔት 2013" (እ.ኤ.አ) በተሰኘው የፍሪደም ሃውስ የኢትዮጵያ ዘገባ መሰረት " በ 2012 (እ.ኤ.አ) በ አይ ሲ ቲ ተጠቃሚዎች ላይ የሚካሄደው (የኢትዮጵያ) ስለላ መጠን ጨምሮ በርከት ያሉ (ሰዎች?) መያዛቸውና ቢያንስ ደግሞ አንድ ሰው መቀጣቱ ተዘግቧል። ሴፕተምበር 2012 (እ.ኤ.አ) የወጣው የቴሌኮም ማጭበርበር ጥፋት ህግ፣ በተራቀቁ የኢንተርኔት "አፕሊኬሽኖች" ላይ የተጣለውን ማዕቀብ አጠናክሯል፣ እንዲሁም በኤሌክትሮናዊ መንገድ የሚላኩ አንዳንድ ይዘቶች በወንጀል አስጠያቂ እንዲሆኑ አድርጓል። ከዚህም በላይ የ"ኦን ላየን" እንቅስቃሴ ክትትል እና የዲጂታል ግንኙነቶች ጠለፋ ተጠናክሯል፣ የፊንስፓይ የክትትል ቴክኖሎጂ በተጠቃሚዎች ላይ በተግባር መሰማራትም በ2013 (እ.ኤ.አ) ተረጋግጧል። [5]

**የፊንስፓይ ጀርባ**

26. ኤግዚቢት " B " "ሁለቴ ብቻ ነው "ክሊክ" የሚያደርጉት- የፊንፊሽር በዓለም ዙሪያ መዳረስ " የተሸኘ የ"ሲትዘንላብ" የማርች 13፣ 2013 (እ.ኤ.አ) ዘገባ ነው። (ፊንስፓይ የጋማ ፊሸር የምርት ዓይነቶች አንዱ ነው።) ዘገባው፣ የፊንፊሸርን የክትትል ለስላስኔ የዕዝና ቁጥጥር "ሰረቨሮች"ን ለይቶ ለማወቅ በኢንተርኔት ላይ የተደረገ ምሉዕ ሉላዊ የኮምፒዩተሮች "ስካን" ውጤቶችን ይገልፃል። ከተቃዋሚዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች በፊንፊሸር አማካኝነት ኢላማ የማድረግ ዘመቻ መገኘቱን በዝርዝር ይገልፃል።

---


4 UNHCR, http://www.unhcr.se/no/media/baltic-and-nordic-headlines/2012/october/12-16-october-2012.html (last visited December 20, 2013).

5 Freedom House, http://www.freedomhouse.org/report/freedom-net/2013/Ethiopia (last visited December 20, 2013).

27. ፊንስፓይ በጋማ ኢንተርናሽናል ግሩፕ ኩባንያዎች ከሚሸጡ የ "አይ ቲ ኢንትሩዥን" ምርቶች አንዱ ነው። የ ጋማ ግሩፕ፣ ለ "ዊንዶውስ፣ ማኪንቶሽ እና ሊነክስ" ኮምፒዩተሮች እዲሁም ለ "አይ ፎን፣ አንድሮይድ፣ ኖኪያ ሲመቢያን፣ ዊንዶውስ ፎን እና በላክቤሪ" የእጅ / ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች የሚሆን የፊንስፓይ ሰላይዌ ያመርታል።

28. ፊንስፓይ ዩናይትድ ኪንግዶም ውስጥ በሚገኘው በጋማ ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና ወይም የጀርመን ኩባንያ በሆነው ፊንፊሸር GmbH (በጋራ "ጋማ") የሚሸጥ የክትትል ለስላስጌ ስብስብ ("ሱይት") ነው። የለስላስጌው ስበስብ፣ ኢላማ ላይ የሚጫን "ክላየንት" ፕሮግራምን፣ አንድ ወይም ካንድ በላይ የፊንስፓይ አቀባባዮችን፣ እና የፊንስፓይ "ማስተር ሰርቨርን" (በጋራ "ፊንስፓይ")፣ ያካትታል። በጋማ የተዘጋጀ የፊንስፓይ ማሻሻጫ "በሮሹር" እንደ ኤግዚቢት " A " ከዚህ ጋር ተያይዟል።

29. የሚከተለው ዲያግራም የፊንስፓይ ለስላስጌ ተግባሩን እንዴት እንደሚያከናውን ያሳያል።




30. ጋማ፣ "ፊንፊሸር "ሶሉዩሽንስ" የሚሸጡት ለመንግስታዊ ድርጅቶች ብቻ ነው" በማለት አበክሮ ይከራከራል።[6]

31. በጋማ ማሻሻጫዎች መሰረት፣ ዘዴው ኢላማ በሆነ መሳሪያ ላይ በሚስጥር ሊጫን በሚችልበት ሁኔታ የተዘጋጀ "ክላየንት" ለስላስጌ (ሰላይዌ)፣ እንዲሁም፣ በሰላይዌው የተሰበሰበሰውን መረጃ ለማሰባሰብ እና ክትትልን ለማቀላጠፍ ስርዓቱን በሚያካሂድ የመንግስት ስራተኛ "ኦፐሬት" የሚደረግ "ኢንፍራስትረክቸር"ን ያካትታል። ሰላይዌው የተጫነባቸው መሳሪያዎች "ኢንፌክትድ ዲቫይስስ" በመባል ይታወቃሉ።

---

[6] FinFisher, http://www.finfisher.com/FinFisher/products_and_services.html (last visited January 9, 2014).

32. ጋማ፣ ፀረ ቫይረስ ፕሮግራም ተብለው በሚታወቁ እጅግ ተወዳጅ በሆኑ 40 ቫይረሶችን እና ስላይጌዎችን ተከታትለው በሚያገኙ ኮምፒዩተር ፕሮግራሞች ላይ ሙከራ ያካሂዳል (እግዚቢት A ን ይመልከቱ)። በፀረ ቫይረስ ፕሮግራሞች ተለይቶ እዳይታወቅ፣ ጋማ ፊንስፓይን ሳያቋርጥ ያሻሽላል። እንዲሁም የማሻሻያውን ውጤት ለፊንስፓይ ደንበኞቹ ያሰራጫል።

33. ጋማ፣ የፊንስፓይ ሰላይጌው እንዳይደረስበትና እንዴት እንደሚሰራ ለማወቅ የሚደረግ ትንታኔን ለማክሸፍ፣ በተወሳሰቡ ቴክኒኮች ይገለገላል። ስለዚህም፣ ፊንስፓይ፣ በተለይ የደህንነት ተመራማሪዎች የሚገለገለሉባቸውን የትንታኔ መሳሪያዎች፣ ሊያዛባ በሚችልበት መልክ ተዘጋጅቷል።

34. ፊንስፓይ የተፃፈው በጋማ በተዘጋጀ ልዩ የፕሮገራም መስሪያ ቋንቋ ነው። ሰላይጌው ተግባሩን እንዲያከናውን በሚደረግበት ጊዜ፣ ቋንቋው ኮምፒዩተሩ ሊገባው ሊፈፅመው ወደ ሚችለው ቋንቋ ይተረጎማል። በሰላይጌው ላይ ማንኛውንም ትንታኔ ለማካሄድ ይኽንን ቋንቋ መረዳትና መፍታት ይጠይቃል። በቋንቋው ላይ ጥቂት ለውጦች በማድረግ ሰላይጌው አጅግ የተለዩ ባህርያት ያሉት እንዲመስል ማድረግ ይቻላል።

35. ከተለከፉ ("ኢንፌክትድ") መሳሪያዎች የተለቀሙ መረጃዎችን ለመሰብሰብ (የሚያገለግለው) "ኢንፈራስተረክቸር" "ፊንስፓይ ማስተር" በመባል የሚታወቀውን ለሰላስኔ እና ጠንካርኔ አካላትን የያዘ እና አንድ ወይም ካንድ በለይ የፊንስፓይ አቀባባዮችን ያካተተ ነው። የፊንስፓይ ማስተሩ ስራ የመረጃ አሰባሰቡን እና የመሳሪያዎቹን ከትትል ማሳለጥ ነው። የፊንስፓይ ማስተሩ ወደ ተለከፈው መሳሪያ ትዕዛዝ ያስተላልፍና የተለቀሙ መረጃዎችን ይቀበላል።

36. የፍንስፓይ ዘዴ የመንግስት ሰራተኛው በተለከፉ መሳሪያዎች ላይ የተለያዩ መረጃዎችን የመከታተልና የመሰብሰብ ተግባሮችን ለማሳለጥ ሊጭን የሚችላቸው "ሞድዩልስ" (የተለያዩ "ፊቸርስ" ያካተቱ አማራጭ ኮምፒዩተር ፕሮግራሞች) አሉት። ለምሳሌ፣ ፊንስፓይ፣ ከ 20 በላይ የተለያዩ የድረ ገፅ "ብራውሰሮች"፣ የ ኢ-ሜይል ፕሮግራሞች እና ወይይት የማካሄጃ ፕሮገራሞች ላይ የይለፍ ቃላትን ("ፓስዎርድስ") ተጠቃሚው በሚተይባቸው ወቅት የይለፍ ቃላቶችን ("ፓስዎርድስ") ስቦ ለማውሰድ የሚያገልግል "ሞዲዩል" አካቷል።

37. እንዲሁም፣ ፊንስፓይ፣ በስካይፐ "አፕሊኬሽን" የሚተላለፉ የኢንተርኔት የስልክ ጥሪዎች፣ "የቴክስት" መልዕክቶች እና የፋይል ማስተላለፎችን ለመቅዳት የሚያገለግል "ሞዲዩል" ፣የስካይፕ ጥሪ በማይደረግበት ጊዜ እንኳን ቢሆን ከኮምፒዩተር ድምፅ ማጉያ ድምፅ ለመቅዳት የሚያስችል "ሞዲዩል"፣ እያንዳንዱን የኮምፒዩተሩ ፊድል ገበታ ቁልፍ ምት በድበቅ የሚቀዳ "ሞዲዩል"፣ እና በኮምፒዩተር "ስክሪን" ላይ የሚታዩ ይዘቶችን ስዕል (ፎረቶገራፍ) ለመቅዳት የሚያገለግል "ሞዲዩል" ይዟል።

38. በተለይ፣ የፊንስፓይ የስካይፐ "ሞዲዩል"፣ ጥሪዎችን ለመቅዳት ስካይፐ ውስጥ ባለ "ፈንክሺናሊቲ" ይገለገላል። በተለይም የስካይፐ ለስላስጌ፣ የስካይፐ የድምፅ ጥሪን መቅዳትን የመሳሰሉ አንዳንድ ነገሮች እንዲያከናውን ሌሎች ለስላስጌዎች እንዲያዙት ይፈቅዳል። የፊንስፓይ የስካይፐ "ሞዲዩል" የስካይፐ የድምፅ ጥሪዎችን የሚቀዳው ጥሪው እየተካሄደ እያለ ሲሆን የሚያካሂደውም ተጠቃሚው ሳያውቅ ወይም ይሁንታውን ሳያገኝ ነው።

39. የፊንስፓይ ሰላይጌ የሚጫነው በ "ሶፍትዌር ኤግዘኪዩተብል" በኩለ ነው። "ኤግዘኪዩተብል" ማለት ማንኛውም ኮምፒዩተሩ ስራ እንዲጀምር የሚያደርግ ( ለምሳሌ "አፕሊኬሽን") የኮምፒዩተር ፋይል ነው። የመንግስት ተወካዩ በማንኛወም ጊዜ በእጁ ("ማኑዋሊ") የፊነስፓይ "ኤግዘኪዩትኤብል" ን በማንኛውም በአካል ወይም ከርቀት ("ሪሞት") ለሊደርስበት ከሚችል ኮምፒዩተር ላይ ሊጭን ይችላል። የመንግስት ተወካዩ በአካል ወይም ከርቀት ሊደርስበት የማይችለው ኮምፒዩተር እንዲለከፍ ከፈለገ፣ ወኪሉ ፊንስፓይ "ኤግዘኪዩተብል" የያዘው የዒላማ ፈይል (ለምሳሌ በ ኢ-ሜይል አማካይነት) በመላክ ኢላማው በራሱ በኢላማው ኮምፒዩተር ላይ እንዲከፍተው ለማሳመን መሞከር ይችላል።

40. የፊንስፓይ "ኦፐሬተሩ" ሊልካቸው የሚችላቸው ፋይሎች፣ በምስል ውስጥ የተሸሸገ የፊንስፓይ "ኤግዘኪዩተበል"" ወይም በማይክሮሶፍት ወርድ ሰነድ ውስጥ የተወሸቀ የፊንስፓይ "ኤግዘኪዩተብል"ን ሊያካትቱ ይችላሉ። የመንግሰት ተወካዩ፣ ፋይሉ ለኢላማው ጠቃሚ ነው በሚል ሰበብ ኢላማው ፈይሉን እንዲከፍት ለማሳመን መሞክር ይችላል። ኢላማው ፋይሉን ሲከፍት፣ እንደ ፋይሉ ዓይነት፣ ትክክለኛ መስል ወይም የ ወርደ ሰነድ ይቀርብለታል።

41. ምስል በሚሆንበት ጊዜ ኢላማውን በማታለል "ኤገዘኪዩተብሉን" እንዲከፍት ይደረጋል፣ እግረ መንገዱንም ይለከፋል። ኤግዘኪዩተብሉ" ራሱን ይሰርዝና እና ለኢላማው በሚታይ ገር ምስል ራሱን ይተካል። ስለዚህ ኢላማው መለከፉን አያውቅም።

42. የ ማክሮሶፍት ሰነድ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሰነዱ በሚከፈትበት ወቅት፣ ሰነዱ ውስጥ የተቀበረው ፊንስፓይ "ኤግዘኪዩተብል" ስራ እንዲጀምር ለማድረግ የሚሞክር "ማክሮ" ይይዛል- "ኦቶሜሽን" እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ የማይክሮሶፍት "ፊቸር"። ተጠቃሚው ከተለከፈ በሁዋላ የወርድ ሰነዱ ራሱን ገር በሆነ ግለባጭ አይተካም። በመሆኑም ሰነዱ እንደገና በሌላ ኮመፒዩተር ላይ ሲከፈት ያንንም ኮምፒዩተር ይለክፈዋል። "ኤግዘኪዩተብሉ" ስራ እንዲጀምር ሲደረግ በኮምፒዩተሩ ዲስክ ላይ ፋይሎችን ለማስቀመጥ የሚጠቀምበት "ዳይሬክቶሪ" ("ፊንስፓይ ዳይሬክቶሪ") ይፈጥራል።

43. እያንዳንዱ የፊንስፓይ 'ኤግዘኪዩተብል" የዚያችን ቅፅበት የሰላይጌ ስራ አፈፃፀም "ፓራሜትሮች" የሚፈለገውን እንዲፈፅሙ የሚያስገድድ የ"ኮንፊጊዩሬሽን" ፋይል ይዟል። በ "ኮንፊጊዩሬሽኑ" ፋይል ውስጥ ተለይተው ከተወሰኑት ("ስፔሲፋይድ" ከሆኑት) "ፓራሜትሮች" መካከል አንዱ፣ ሰላይጌው ሊገናኛቸው የሚገባው የፊንስፓይ ማስተሮችን የሚወክሉ የአንድ ወይም ከአንድ በለይ የሆኑ የኢንተርኔት አድራሻዎች ወይም የኢንተርኔት ዶሜየን" ስሞች ዝርዝር ነው።

44. ጋማ፣ በ አንድ ጊዜ / በ አንድ ላይ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው የተለከፉ መሳሪያዎች ብቻ ክትተል እንዲደረግባቸው የሚያስችል ሊቼንሳ ይሸጣል (ኤግዚቢት A ን ይመልከቱ) ። ቁጥሩ የሚወሰነው በጋማ እና በመንግስቱ የፊንስፓይ "ኦፐሬተር" መካከል በሚደረግ ሊቼነሳ ስምምነት መሰረት ነው።

45. መሳሪያው በፊንስፓይ ሲለከፍ፣ በ "ኮንግፊዩሬሽን" ፋይሉ ውስጥ በተዘረዘሩ አቀባባዮች አማካይነት ከፊንስፓይ ማስተሩ ጋር ግንኙነት ይፈጥራል። የተለከፉት መሳሪያዎች ቁጥር ለክትትል ሊቼንሳ ከተሰጣቸው ከከፍተኛው ቁጥር ያነሰ ከሆነ፣ ልክፍቱ "አክቲቭ" ይሆናል። በአንድ ጊዜ ክትትል የሚደረግባቸው መሳሪያዎች ቁጥር ባንድ ጊዜ ክትትል እንዲደረግባቸው ከተፈቀደላቸው መሳሪያዎች ከፍተኛ ቁጥር እኩል ከሆነ፣ ልክፍቱ "እንዳንቀላፋ ይቀራል። ቢሆንም ግን የተለከፉት መሳሪያዎች ቁጥር ከደፉ ("ትሬሽሆልድ") በታች ወርዶ እንደሆን ለማረጋገጥ አልፎ አለፎ ከ ፊንስፓይ ማስተር

"ሰርቨር" ጋረ ግንኙነት ያደርጋል። ይኽ በሚሆንበት ጊዜ ወይም የመንግስት ሰራተኛው ተጨማሪ ሊቼንሳዎች ከጋማ በሚገዛበት ጊዜ "ልክፍቱ ተመልሶ "አክቲቨ" ይሆናል።

46. አንድ ልክፍት "አክቲቨ" ሲሆን፣ "ሞዲዩሎቹን" ለማራገፍ ("ዳውንሎድ") ከፊንስፓይ አቀባባዮች ጋር ግንኙነት ይፈጥርና መረጃ በመሰብሰብ ወደ ፊንስፓይ ማስተር መላክ ይጀምራል። የፊንስፓይ አቀባባይ፣ በተራው፣ ወደ ተለከፈ መሳሪያ ትዕዛዝ መላክ ይችላል።

47. በመረጃ እና እምነት መሰረት፣ እነዚህ ትዕዛዞች፣ በተለከፈ መሳሪያ ላይ ያለውን ሰላይጌ ከርቀት "ዲአክቲቬት" የማድረግ ችሎታን ያካትታሉ (ኤግዚቢት A'ን ይመልከቱ)። ትዕዛዞች፣ የመንግስት "ኦፐሬተሩ"ን፣ አዲስ የኢንተርኔት አድራሻ ወይም የ"ዶሜይን" ስምን የፊንስፓይ አቀባባይ ለማድረግ፣ በተለከፈ መሳሪያ ላይ "ከስተም" ፕሮግራሞች እንዲሰሩ ለማድረግ፣ መሳሪያው ላይ የተቀመጡ መረጃዎችን ለመመልከት፣ እና ከ መሳሪያው የድምፅ ማጉያ ላይ "ላይቭ" የድምፅ ቅጂዎችን የመሳሰሉ "ፍቸሮችን" ለማስነሳትና ለማጥፋት ያስችሉታል።

48. የስካይፐ ጥሪዎች "ሞዲዩሎችን" ጨምሮ፣ አብዛኛዎቹ የፊንስፓይ "ሞዲዩሎች" ከዚህ በሚከተለው ዓይነት ይሰራሉ: የፊንስፓይ "ሞዲዩሉ"፣ መረጃ ወደ ፊንስፓይ ማስተር ከማስተላለፉ በፊት፣ መረጃው እየተጠለፈ እያለ በተለከፈው ከሞመፒዩተር ጠንካርዲስክ ለይ ይፅፈዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ እንደ ፊንስካይፐ "ሞዲዩሉ" ጉዳይ በመሳሰሉት፣ መጀመሪያ "ሞዲዩሉ" መረጃውን በኮምፒዩተሩ ጊዜያዊ የዲስክ ማህደር ውስጥ ያሉት ፋሎች ላይ ሚስጥር ኮድ ውስጥ ሳይከት ይፅፋል። ከዚያ፣ "ሞዲዩሉ"፣ መረጃውን በሚስጥር ኮድ ያደርገውና የተጠለፉ መረጃዎችን የያዙ ፋይሎችን በሚለይ የስያሜ "ኮነቬንሽን" በመጠቀም፣ ፊንስፓይ ዳይሬክተሪ ውስጥ ወደሚገኝ ሚስጥር ኮድ ወስጥ የገባ ፋይል ላይ ይፅፈዋል።

49. ለምሳሌ፣ በፊንስፓይ የስያሜ "ኮንቬንሽን" ስር ፣ በስካይፐ ጥሪ ወቅት የተቀዱ ገቢ ድምፆችን የያዙ ፋይሎች በ "snd" ይጀምሩና በአንድና በአራት መካከል ባሉ "ሄክሳዴሲማል" "ዲጂቶች" ይጨርሳሉ። "ሄክሳዴሲማል" "ዲጂታል"፣ 0-9 ከዜሮ አሰከ ዘጠኝ ያሉ እሴቶችን የሚወክሉበት እና A፣ B፣ C፣ D፣ E፣ F (ወይም በተለዋጩ a–f) ከ 10 አስከ 15 እሴቶችን የሚወክሉበት፣ የቤዝ-16 ቁጥር ነው።

50. በጣም መልካም በሆነ ሁኔታ ውስጥ ፣ የሚስጥር ኮድ ውስጥ የገባው ፋይል በተሳካ ሁኔታ ከተፃፈ በሁዋላ ግዚያዊ ፋይሉ ይሰረዛል (ይደመሰሳል)። ይሁንና እና፣ አንዳንድ ጊዜ፣ ፊንስፓይ ጊዜያዊ ፋይሎችን መሰረዝ እነደሚሳነው የደህንነት ተመራማሪዎች አስተውለዋል።

51. ፊንስፓይ፣ ቤየጊዜው፣ ከተጠለፉ መረጃዎች የስያሜ "ኮንቬንሽን" የሚገጣጠሙ ፋይሎችን በሙሉ ወደ ፊንስፓይ ማስተር ያስተላልፋል። ፊንስፓይ በተሳካ ሁኔታ እነዚህን ፋይሎች ካስተላለፈ በሁዋላ ይሰርዛቸዋል።

52. በተለመደው አሰራር፣ ማንኛውም ፕሮግራም በኮምፒዩተር ጠንከዲስክ ላይ ፋይል በሚፅፍበት ጊዜ፣ ኮምፒዩተሩ አወቶማቲክ በሆነ መንገድ ፋይሉ የተፃፈበትን ቀን እና ሰዓት ይመዘግብና ቢያንስ የመጨረሻወን ቀን (ከፋይሉ ጋር) ያኖራል- አንዳንድ ጊዜ ቀደም ያሉ ቀናትም ይከማቻሉ።

53. በአንዳንድ ሁኔታዎች ፊንስፓይ በሂደቱ ውስጥ ጣልቃ በመግባት የፃፋቸውን አንዳንደ ፋይሎች ልክ ከአንድ ዐመት በፊት እንደተፃፉ አድርጎ እንደሚያሳይ የደህንነት ተማራመሪዎች አስተውለዋል። እንዲህ ዓይነቱ ቀናትን ወደሁዋላ የማድረግ ተግባር በአንዳንድ ሁኔታዎች "ልከፊቶች" እንዳይታወቁ ትንሽ ለማካበድ የተሰራ የፊንስፓይ "ፊቸር" ስለመሆኑ ከሳሽ መረጃ አለው፣ ያምንበታልም።

54. አንድ መሳሪያ በ ፊንስፓይ ሲለከፍ፤ ልክፍቱ አለቅ ብሎ ሊቆይ ይችላል- ኮምፒዩተሩ ጠፍቶ ሲነሳ፣ አሁንም በፊንስፓይ እንደተለከፈ ነው ማለት ነው። ይኽ ሊከናወን የሚችልበት አንዱ ሁኔታ የኮምፒዩተሩን የማስነሻ ሂደት ለየት በማድረግ ነው።[7] ሰላይጌው ራሱን የሚያስቀምጠው ለወትሮው አገልግሎት ላይ በማይውለው እና የኮምፒዩተሩ የ"ኦፐሬቲንግ" ዘዴ ለወትሮው ("ቲፒካሊ) የማይደርስበት የዲስክ ክፍል ውስጥ ነው። ይኽ ያልተከፋፈለ ቦታ በመባል ይታወቃል። ከኮምፒዩተሩ "ኦፐሬቲንግ" ዘዴ አስቀድሞ ፊንስፓይ እንዲጫን የኮምፒዩተር ማስነሻ ዘዴው ይሻሻላል። የኮምፒዩተሩ "ኦፐሬቲንግ" ዘዴ እየተጫነ ባለበት ሰዓት፣ ፊንስፓይ "ኦፐሬቲንግ" ዘዴውን ይለክፈዋል። ስለዚህ፣ ፊንስፓይ

---

[7] የኮምፒዩተር ማስነሳት ሂደት ማለት ኮምፒዩተሩ "ኦፐሬቲንግ ሲስተሙን" ለመጫን እንዲነሳ ሲደረግ አውቶማቲክ በሆነ መንገድ የሚወስዳቸው ተከታታይ እርምጃዎች ናቸው፣ ለምሳሌ ማይክሮሶፍት ዊንዶውስ።

ለወትሮው ከሚታዩትና ሊደረስባቸው ከሚችሉት የዲሰኩ አካባቢ ቢወገድም፣ ኮምፒዩተሩ እንደገና ሲነሳ የማስነሻው ዘዴ አሁንም ኮመፒዩተሩን እንደገና ይለክፈዋል።

### በተለይ የከሳሹ ኮምፒዩተር በፌንስፓይ ስለተለከፈበት

55. በማርች 2013 (እ.ኤ.አ) ወይም በዚያ አካባቢ፣ በከሳሹ ኮምፒዩተር ወስጥ የሚገኘው ዲስክ ሁለት የማይክሮሶፍት ፋይሎች GKO2.doc እና GKO2 (1).doc ነበሩበት፣ እነርሱ ደግሞ በተራቸው በማይክሮሶፍት ዊንዶውስ የሚሰሩ ኮምፒዩተሮችን ለመልከፍ የተዘጋጁ የፌንስፓይ "ኤግዚኪዩተብልስ" ነበሩባቸው።

56. ፋይሎቹ ኮምፒዩተር ላይ ሲከፈቱ፣ በማይክሮሶፍት ወርድ የተፃፉ በርከት ያሉ የአማርኛ[8] ፓረግራፎች ያሳያሉ (ኤግዚቢት C ን ይመልከቱ፣ ወናውን የዎርድ የቴክስት ሰነድ እና ተጓዳኝ የኢንግሊዝኛ ትርጉሙን ጨምሮ ለከሳሽ "ፎርዎርድ" የተደረገ ኢ-ሜይል)። ያኔውኑ ሰነዱ ውስጥ የሚገኝ "ማክሮ" የተጠቃሚውን ኮምፒዩተር በፌንስፓይ ለማስለከፍ ይሞክራል። በነዚህ ፋይሎች ላይ የነበሩት ቀናት፣ እንደ ቅደም ተከተላቸው፣ ኦክተበር 31፣2012 (እ.ኤ.አ) በ 09:25:17 እና ኦክተበር 31፣2012 (እ.ኤ.አ) በ 09:25:46 ነበሩ።

57. በማርች 2013፣ ወይም በዚያው አካባቢ፣ በከሳሹ ኮምፒዩተር ላይ በነበሩት GKO.doc እና GKO (1).doc ውስጥ የፌንስፓይ ግልባጭ ነበረባቸው።

58. ይኸ የፌንስፓይ ግልባጭ፣ ላንድ ብቸኛ የፌንስፓይ አቀባባይ፣ የኢንተርኔት ፕሮቶኮሉ ("አይ ፒ")[9] አድራሻ 213.55.99.74 የሆነ "ኮንፊጊዩሬሽን" ፋይል የዞ ነበር።

59. 213.55.99.74 አድራሻ የተከሳሹ ኢትዮጵያ የመንግስት ንብረት በሆነው ቴሌኮሙኒኬሽን ኩባንያ -[10] [11][12]ኢቲዮ ቴሌኮም- ስም ከተመዘገቡ የአድራሻዎች ስበስብ ውስጥ ነው።

---

[8] አማርኛ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑበሊክ የይፋ የስራ ቋንቋ ነው

[9] የ አይ ፒ አድራሻ የአንድ ወይም የበርካታ ኮምፒዩተር/ሮችን የ"ኔትዎርክ" አድራሻ ባንተርኔት ውስጥ የሚገኝበትን ስፍራ ለማወቅ አገልግሎት ላይ የሚውል አሀዛዊ እሴት ነው። ባንተርኔት ላይ ያለ ማንኛውም ኮምፒዩተር ከሌሎች ኢንተርኔት ላይ ካሉ ኮምፒዩተሮች ጋር ለመገናኘት የ አየይ ፒ አድራሻ ያስፈልገዋል።

[10] የ አይ ፒ አድራሻዎች የሚመደቡት / ሚታደሉት፣ በዓለም ዙሪያ ከተከማቹ አራት ሚልዮን ያኸል ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ አድራሻዎች ለትርፍ በማይሰሩ ጆግራፊያዊ ድርጅቶች በኩል የሚመደቡት ተከታታይ ቁጥር ባላቸው ስብስቦች መልክ ነው።

60. በመረጃ እና በእምነት መሰረት፣ ይኸ አቀባባይ የሚገኘው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው፣ እና ተገልጋዩም የ ኢትዮ ቴሌኮም ደንበኛ ወይም "ሰብስክራይበር" ነው።

61. የደህንነት ተመራማሪዎች፣ የተለያየ የኢንተርኔት ቁጥር ያላቸውን አድራሻዎች "ስካን" አድርገዋል። በዚህ ዓይነት በተደረገ አንድ "ስካን" ምክንያት፣ 213፣55፣99፣74 ላይ የፊንስፓይ አቀባባይ መኖሩ የደህንነት ኩባንያ በሆነው በ ራፒድ ድረ ገፅ ላይ በወጣ የምርምር "በሎግ" ላይ በኦገስት 8፣2012 ለመጀመሪያ ጊዜ ተገለፀ።[13]

62. ይኸን ተከትሎ ሲትዘንላብ ያካሄደው "ስካን" የ 213.55.99.74 አድራሻ የፊንስፓይ አቀባባይ መሆኑን አረጋገጠ። እነዚህ ውጤቶች ኦገስት 29፣ 2012 (እ.ኤ.አ) እና ማርች 13፣ 2013 (እ.ኤ.አ) ይፋ ተደርገዋል (ኤግዚቢት Bን *ይመልከቱ*)። ሁለቱንም ጊዜ፣ በህትመቱ ወቅት አቀባባዩ ገና "ኦፐሬሽናል" ነበር።

63. የማርች 13፣ 2013 (እ.ኤ.አ) የሰሲትዘንላብ ህተመት ያንንው የኢትዮጵያ አቀባባይ "ኮንፊጊዩሬሽን" ፋይል የያዘ እና በኢትዮጵያ ተቃዋሚ አመራሮችን ምስል ውስጥ የተሸሸገ የፊንስፓይ "ኤግዘኪዩትብል" መገኘቱን ዘግቧል (ኤግዚቢት B ን *ይመልከቱ* )።

64. በከሳሹ ኮምፒዩተር ላይ ያለው ጠንከርዲስክ ስማቸው ከፊንስፐይ የስያሜ "ኮነቬንሽን" ጋር የሚሄዱ (አንደ ዓይነት የሆኑ) በርከት ያሉ ገዜያዊ ፋይሎች ይዟል።

65. አነዚህን ፋይሎች ፈጥሮ፣ ተከሳሹ ሳያወቅና ይሁንታውን ሳይሰጥ፣ ኮምፒዩተሩ ላይ "ሴቭ" ያደረገው የፊንስፓዩ ለስላስጌ ነው።

---

[11] Rapid7, Information Security: Analysis of the FinFisher Lawful Interception Malware, https://community.rapid7.com/community/infosec/blog/2012/08/08/finfisher (last visited November 13, 2013).

66. በለተይም፣ በከሳሽ ኮምፒዩተር ውስጥ የሚገኘው ጠንከርዲስክ ስማቸው በ“snd” የሚጀምርና በ አንድና በአራት ሄክሳዴሲማል ዲጂቶች መካከል የሚያልቅ 244 ፈይሎችን ይዟል። ፊንስፓይ በስካይፐ ጥሪ ወቅት የሚመጣ ድምፅን ለመቅዳት በዚህ የስያሜ "ኮንቬንሽን" የገለገላል።

67. ጠንከርጌው፣ ስማቸው በ “mic” የሚጀምር እና ከአንድ እስከ አራት "ሄክሶዴሲማል" "ዲጂትስ" የሚጨርስ 247 ፋይሎች ይዟል። ፊንስፓይ በዚህ የስያሜ "ኮንቬንሽን" በስካይፐ ጥሪ ወቅት የሚወጣ ድምፅን ለመቅዳት የገለገልበታል (ወጭ ድምፅ)።

68. የፊንስፓይ የሰላይጌ "ሞዲዩል" ስራውን የሚያከናውነው እንደሚከተለው ነው፡ በተለያዩ ጊዜያት ሁለት የድምፅ ልቁቶችን - ገቢና ወጭ- ከቀዳ በሁዋላ፣ ሁለቱ ልቁቶች ይጣመሩና አንድ ፋይል ይሆናሉ፡፡ ገቢው ድምፅ በ "ስቲሪዎ" ጣቢያው ቀኝ እንዲሆን የደረጋል እንዲሁም ወጭው ፋይል በ "ስትሪዎ" ጣቢያው በስተግራ እንዲሆን ይደረጋል። ከዚያ ቀጥሎ መጠኑን ለመቀነስ ፋይሉ ይታመቃል። ፊንስፓይ፣ የዚህን ሂደት ውጤት፣ ስሙ በ “ogg” በሚጀምር እና ከአንድ እስከ አራት "ሄክሶዴሲማል" "ዲጂት" በሚጨርስ ግዜያዊ ፋይል ውስጥ ያከማቸዋል።

69. በከሳሹ ኮምፒዩተር ውስጥ የሚገኘው ጠንካርዲስክ 83 የዚሁ ዓይነት ከፊንስፓይ የስያሜ "ኮነቬንሽን" ጋር የሚጣጣሙ “ogg” ፋይሎች ይዟል። እነዚህ ፋይሎች የከሳሹን የግልና እጅግ ሚስጥራዊ የሆኑ የስካይፐ ውይይቶችን ከፊል ወይም ሙሉ ግልባጮችን የያዙ ኛቸው።

70. በከሳሹ ኮምፒዩተር ላይ የተገኙት የፊንስፓይ ልክፍት ርዝራዦች በአንድ ላይ "ፊንስፓይ ትሬስ ፋይልስ" በመባል ይታወቃሉ።

71. በጣም መልካም በሆነ ሁኔታ ባለበት ጊዜ፣ ፊንስፓይ በነዚህ ጊዜያዊ ፋይሎች ተጠቅሞ ከጨረሰ በሁዋላ ይሰርዛቸዋል። የ “snd”፣ “mic"፣ እና “ogg” ፋይሎች መኖር በፊንስፓይ ከተቀዱ የስፓይክ ጥሪዎች ጋር የተስተካከለ ("ኮንሲስተንት") ነበር። እንዲሁም በፊንስፓይ የወትሮ አሰራር ፋይሎቹ በፊንስፓይ አቀባባይ አማካይነት ወደ ፊንስፓይ ማስተር ይተላለፉ ነበር ( የፊንስፓይ አቀባባይ እንዴት እንደሚሰራ ለማየት ኤግዚቢት A ን *ይመልከቱ)*።

72. በየትኞቹም የፊንስፓይ ርዝራዥ ፋይሎች ላይ በቀዳሚነት የታየው ቀን ዲሴምበር 7፣ 2011 (እ.ኤ.አ) በ 09፡35፡48 ነበር።[14] ይህ ፋይል፣ ከተስተዋሉ የፊንስፓይ ባህርዮች ጋር በተስተካከለ ("ኮነስስተንት")መልኩ ቀኑ ልክ በአንድ ዐመት ወደሁዋላ እንዲሆን የተደረገ ይመስላል። በየትኞቹም የፊንስፓይ ርዝራዥ ፋይሎች ላይ ለመጨረሻ ጊዜ የታየው ቀን ማርች 17፣ 2013 (እ.ኤ.አ) በ 17፡30፡35 ነበር።

73. ፊንስፓይ ስማቸው በ "del" የሚጀምር እና ከአንድ እስከ አራት ባሉ "ሄክሶዴሲማል" "ዲጂቶች" የሚጨርስ ጊዘያዊ ፋይሎችንም ያከማቻል። ዲስኩ 1597 እንዲህ ዓይነት ፋይሎችን ይዟል። በእነዚህ ሁሉ ፋይሎች ላይ ለመጨረሻ ጊዜ የታየው ቀን ማርች 18፣ 2013 (እ.ኤ.አ) በ 08፡58፡24 ነበር።

74. በከሳሹ ኮምፒዩተር ውስጥ የሚገኘው ዲስክ፣ ኮዱን ጨምሮ፣ የተለያዩ የፊንስፓይ አካለትን፣ "ኮንፊጊዩሬሽን" ፋይሎች፣ እና የተሰበሰበ መረጃ የያዙ እና በሚስጥር ኮድ ውስጥ የገቡ ፋይሎችን ከመላካቸው በፊት ለማከማቸት ፊንስፓይ የተገለገለበትን " ProtectedSvc" ፎልደር ይዟል።

75. በፎልደሩ ላይ ያለው ቀን ኦክቶበር 31፣ 2011 (እ.ኤ.አ) በ 09፡26፡39 ነበር። በመረጃ እና እምነት መሰረት፣ የ "ProtectedSvc" ፎልደሩ ቀን፣ በፊንስፓይ፣ ልክ በአንድ ዐመት ወደሁዋላ ተመልሶ ነበር። ስለሆነም ከሳሹ፣ ተከሳሽ ኢትዮጵያ ኮምፒዩተሩን የለከፈችበት ቀን ኦክተበር 31፣ 2012 (እ.ኤ.አ) እንደነበር መረጃ አለው፣ ያምናልም።

> በከሳሹ ኮመፒዩተር ላይ ያለው ProtectedSvc ፎልደር፣ የፊንስፓይ ኮድ፣ የ "ኮንፊጊዩሬሽን ፋይል፣ እና ወደ "ሰርቨሩ" ሳይላኩ የቀሩና የተሰበሰበ መረጃ የያዙ በርካታ ሚስጥር ኮድ ውስጥ የገቡ ፋይሎችንም ይዟል። ከፎልደሩ ጋር በተያያዘ በጣም የቀረበው ቀን ማርች 18፣ 2013 (እ.ኤ.አ) በ 08፡58፡27 ነው። ይህም በከሳሹ ኮምፒዩተር ላይ ካለ ከማንኛውም ፋይል ጋር ከተዛመደ በፊንስፓይ ከተፃፈ ወይም የፊንስፓይ ንብረት ከሆነ ፋይል ጋር የሚጣጣም እጅጉን የቀረበው ቀን ነው። ይኽ፣ በተከሳሹ ምርጥ ግምት፣ በተከሳሹ ኮምፒዩተር ላይ የፊንስፓይ እንቅቅስቃሴ የተደረገበት የመጨረሻ ቀን ነው።

76. ለማጠቃለል ያህል፣ ኦክተበር 31፣ 2012 (እ.ኤ.አ) በ 09፡26፡39 የከሳሽ ኮምፒዩተር በፊንስፓይ ተለከፈ። ከሰርቨሩ የተራገፉ "ሞጁዩሎች" ከያዙ ፋይሎች ጋር የተያያዘው ከሁሉ የቀደመ ቀን ኖቬምበር 12፣ 2011 (እ.ኤ.አ) ፣ 08፡23፡14 ነው። ይኽ ከፊንስፓይ ቀናትን ወደሁዋላ ለክ በአንድ ዓመት የመመለስ ቴክኒክ ጋር የተስተካከለ ነው። ስለዚህም ልክፍቱ "አክቲቭ" የሆነበት ቀን ምርጥ ግምት ኖቬምበር 12፣ 2012 (እ.ኤ.አ) በ 08፡23፡14 ነው። ልክፍቱ፣ ኢትዮጵያ

---

[14] ሰ ዓቶቹ በሙሉ "ኢስተርን" ናቸው። እንዲሁም የ 24 ሰዓት አቆጣጠር ደንብን በመከተል የተፃፉ ናቸው።

በፊንስፓይ ሰለመጠቀሟ እና ኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ላይ ስለዋለው የፊንስፓይ አቀባባይ ቴክኒካዊ ዝርዝር የሚዘግበው የሲትዘንላብ ዘገባ ታትሞ በወጣ በአምስት ቀናት ውስጥ ብቻ፣ ማርች 18፣ 2013 (እ.ኤ.አ) በ 08፡58፡27፣ የተነሳ ይመስላል።

## <u>የክስ ማጠቃለያ</u>

77. ጋማ የፊንስፓይ ምርቶችን የሚሸጠው ለህግ አስከባሪና ለስለላ ድርጅት ነው የሚል በግልፅ አቋም ይዟል።

78. ተከሳሽ ኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያን የህግ አስከባሪና የስለላ ድርጅቶች በሙሉ ትቆጣጠራለች።

79. በመረጃ እና በ እምነት መሰረት፣ ጋማ የፊንስፓይ ለስላስጌ ስብስብ ("ሱዊይት") ለተከሳሽ ኢትዮጵያ ሽጧል።

80. ተከሳሽ ኢትዮጵያ ሆን ብላ በፊንስፓይ የተለከፈ የወርድ ሰነድ አሰራጭታለች።

81. የከሳሽ ኮምፒዩተር ኦክተበር 31፣ 2012 (እ.ኤ.አ) በ 09፡26፡39 ወይም በዚያ አካባቢ፣ በማይክሮሶፍት ዎርድ ፋይል አማካይነት በፊንስፓይ ተለከፏል።

82. ፊንስፓይ በከሳሹ ኮምፒዩተር ላይ መጫኑ፣ ሆን ብሎ በተዘጋጀ የማይክሮሶፍት ፋይል አማካይነት ኢትዮጵያ ሆን ብላ እንድትለክፈው አደረገ።

83. በከሳሽ ኮምፒዩተር ላይ የተጫነው ፊንስፓይ በኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ባሉ የ አይ ፒ የአደራሻዎች ስብስብ ውስጥ ካለ የፊንስፓይ አቀባባይ ትዕዛዝ ተቀብሏል።

84. በመረጃ እና እምነት መሰረት፣ የተከሳሹን ኮምፒዩተር ቁጥጥር ስር ያዋሉት የፊንስፓይ አቀባባይና የፊንስፓይ ማስተር "ሰርቨሮች" ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ እና በተከሳሽ ኢትዮጵያ ቁጥጥር ስር ያሉ ነበሩ።

85. በኖቬምበር 12፣ 2012 (እ.ኤ.አ) በ08፡23፡14 ወይም በዚያ አካባቢ፣ በከሳሹ ኮመፒዩተር ላይ የተጫነ ፊነስፓይ ከዚህ ፊንስፓይ ማስተር "ሰርቨር" ወደ ተከሳሹ ኮምፒዩተር "ሞዲዩሎችን" አራገፈ።

86. በመረጃ እና በእምነት መሰረት፣ የፊንስፓይ ለስላስጌው በተከሳሽ በኢትዮጵያ ትዕዛዝ፣ የከሳሽን ግንኙነቶች ለመጥለፍ በተራገፉት "ሞዲዩሎች" ተጠቅሟል።

87. የፊንስፓይ "አፐሬተሩ"፣ ሲትዘንላብ በኢትዮጵያ "አፐሬት" የሚደረገውን እና የከሳሹን ኮመፒዩተር የሚቆጣጠረውን የፊንስፓይ አቀባባይ የሚገልፅ ቴክኒካዊ ዝርዝር ዘገባ አትሞ ባወጣ በአምስት ቀናት ውስጥ ብቻ፣በማርች 18፣ 2013 (እ.ኤ.አ) በ 08፡58፡27 ወይም በዚያ አካባቢ፣ ከከሳሽ ኮምፒዩተር ላይ የፊንስፓይ ለስላስጌ ልክፍቱን ለማንሳት ሞከረ።

በመረጃ እና በዕምነት መሰረት፣ በከሳሹ ኮምፒዩተር ላይ የተጫነው ፊንስፓይ ተከሳሽ ኢትዮጵያ ቦክተበር 2012 (እ.ኤ.አ) እና ማርች 2013 (እ.ኤ.አ) መካከል በነበሩት ጊዜያት በሙሉ፣ በተከሳሽ ቁጥጥር ስር ነበር።

## <u>አንደኛ የክስ ምክንያት</u>

### የ "ዋየርታፐ" የህግ ድንጋጌ 18 ዩ ኤስ ሲ § 2511 ን መተላለፍ

88. ተከሳሹ በዚህ አቤቱታ በቀደሙት ፓራግራፎች ውስጥ የተባሉትን እዚህም የደግማል፣ በማጣቀስም እዚህ ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲካተቱ ያደርጋል።

89. የ ዋየርታፐ የህግ ድንጋጌ፣ ማንኛውንም የሽቦ፣ የቃል፣ ወይም የኤሌክትሮኒክ ገንኙነቶችን አስቦ መጥለፍን ይከለክላል።

90. 18 ዩ ኤስ ሲ § 2520 የግል የመክሰስ መብት ይሰጣል። ይኸ መብት "ለማንኛውም የሽቦ፣ የቃል፣ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቱ ለተጠለፈበት፣ ለተጋለጠበት ወይም ሆን ብሎ ጥቅም ላይ ለዋለበት ማንኛውም ሰው" የሚያገልግል ነው።

91. ተከሳሽ ሆን ብሎና አስቦ የከሳሽን የሽቦ፣ የቃል፣ ወይም ያሌክትሮኒክ ግንኝነቶች ጠልፏል።

92. በተከሳሹ ከተጠለፉ ሌሎች መረጃዎች ውስጥ የከሳሽ የስካይፐ ጥሪዎች፣ በዋየርታፐ የህግ ድንጋጌ ትርጉም መሰረት፣ የሽቦ፣ የቃል፣ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶች ነበሩ።

93. ተከሳሽ ኢትዮጵያ በፊንስፓይ በመጠቀም፣ የተከሳሹን የስካይፕ የስልክ ጥሪዎች ለማግኘት መቻሉ፣ በዋየርታፕ የህግ ድንጋጌ ትርጉም መሰረት ጠለፋ ነው። ምክንያቱም የከሳሽ ግንኙነቶች ይዘት ሊገኝ የቻለው በማንኛውም ኤሌክትሮኒክ፣ ሜካኒካል ወይም ሌላ መሳሪያ በመጠቀም ስለሆነ ነው።

94. ተከሳሹ የሽቦ፣ የቃል፣ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶቹ የብቻው ብቻ ሆነው ይቀራሉ የሚል የአእምሮ ግምት ነበረው

95. በ 18 ዩ ኤስ ሲ § 2520 መሰረት፣ ከሳሽ የሽቦ፣ የቃል፣ ወይም የኤሌክትሮኒክ ገንኙነቶቹ የተጠለፉበት ሰው ነው።

96. አንቀፅ 2520፣ ለእያንዳንዱ የዋየርታፕ የህግ ድንጋጌ ጥሰት፣ በህግ ከተወሰነ የ$ 10,000 ወይም $ 100 በቀን ካሳ በተጨማሪ፣ ፍትሃዊ እና "ዲክላራቶሬ" ፋታ / ፍርድ ይደነግጋል።

<u>ሁለተኛ የክስ ምክንያት</u>

**በብቻነት ላይ ጣልቃ መግባት**

97. ተከሳሹ በዚህ አቤቱታ በቀደሙት ፓራግራፎች ውስጥ የተባሉትን እዚህም የደግማል፣ በማጣቀስም እዚህ ውስጥ ሙሉ በሙሉ እንዲካተቱ ያደርጋል።

98. ተከሳሽ ሆን በሎ በከሳሽ የብቻነት እና ብቸኝነት / መገለል ላይ ጣልቃ ገብቷል።

99. ተከሳሽ የከሳሽን የግል ጉዳዮች እና ገመናዎች ላይ ጣልቃ ገብቷል።

100. የከሳሽ የግል ጉዳዮች እና ገመናዎች፣ በተከሳሽ የተጠለፉት የሽቦ፣ የቃል፣ ወይም የኤሌክትሮኒክ ግንኙነቶችን ጨምሮ፣ ማህበረሰባዊ / ሕዝባዊ ስጋቶች አይደሉም።

101. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት በብቻነት ላይ የተፈፀሙ ጣልቃ ግብነቶች፣ ለተራ እና የአእምሮ ግምት ላለው ሰው አፀያፊ ናቸው።

## የፍርድ ልመና

ስለዚህም ከሳሹ፥

1. ከላይ የተገለፁት የተከሳሽ ድርጊቶች የዋየርታፕ የህግ ድንጋጌዎች የጣሱ እና በብቻነት ለይ ጣልቃ መግባት ናቸው ብሎ እንዲወስን፣
2. ተከሳሹ ባደረሰበት በደል ምክንያት ከሳሹ ለደረሰበት ጉዳት  በህግ የተወሰነውንም ጨምሮ፣ በፍርድ ሂደቱ ወቅት በማስረጃ በሚረጋገጠው መሰረት፣ ካሳ እና ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ የሚጀምር ወለድን የሚጨምር ውሳኔ እንዲሰጥ፣
3. በአእምሮ ግምት በቂ የሆነ የጠበቃ እና ሌሎችንም የክስ ኪሳራዎችና ወጭዎች በህግ እስከተወሰነው መጠን ድረስ ለከሳሽ እንዲወስን፣ እና
4. ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምነውን ሌላ እና ተጨማሪ ካሳ እንዲሰጠው እንዲፈቅድ፣

ፍርድ ቤቱን ይለምናል።

## የፍርድ ሸንጎ ጥያቄ

በፍርድ ሸንጎ ሊዳኙ የሚችሉ ጉዳዮች ሁሉ በፍርድ ሸንጎ እንዲታዩለት እንዲደረግ በዚሁ ይጠይቃል።

Dated: February 18, 2014

Respectfully submitted,

______________________________

Mitchell L. Stoltz (DC SBN 978149)
ELECTRONIC FRONTIER FOUNDATION
815 Eddy Street
San Francisco, CA 94109
Tel.: (415) 436-9333
Fax: (415) 436-9993
mitch@eff.org

Richard M. Martinez (*pro hac* pending)
Samuel L. Walling (*pro hac* pending)
Mahesha P. Subbaraman (*pro hac* pending)
ROBINS, KAPLAN, MILLER & CIRESI L.L.P.
2800 LaSalle Plaza
800 LaSalle Avenue

Minneapolis, MN 55402-2015
Tel.: (612) 349-8500
Fax: (612) 339-4181
rmmartinez@rkmc.com

Counsel for Plaintiff